# መልአከ ብርሃን አድማሱ ጀንበሬ

/፲፰፻፹፰ – ፲፱፻፷፪/

*በአሥራት ከበደ*

ቤተ ክርስቲያን ሆይ ኦርቶዶክሳዊት፣
ጠበቃሽ ተረታ ሐምሌ ሃያ አራት፣
መጋቤ ምሥጢራት የሊቆቹ ዋልታ፣
መልአከ ብርሃን መዓርገ ጌታ፣
ትምህርትን ጋባዡ በሰፊ ገበታ፣
የመጻሕፍት ምንጭ ማፍለቅ እማይገታ፣
አንደበተ ዕንቊ አፈ ወርቅ አለኝታ፣
የሕግ መሐንዲስ ለሃይማኖት ካርታ፣
ለተጋፊው ሁሉ መናፍቅ ወስላታ፣
በሚያስደንቅ ትግል እንዲያ ሲበረታ፣
በሐምሌ ሃያ አራት ደከመው ተረታ።

*አለቃ ተገኝ ታምሩ*
*ጐጃም ዘደብረ ኤልያስ*



*ትልቅ እምነት ከሊቅነት ጋር አጣምረው የኖሩት መልአከ ብርሃን አድማሱ ጀንበሬ*

ከአርባ ቀን መታሰቢያ ከቀረበ ግጥም የተወሰደ ነው። በ፲፱፻፵፩ ዓ.ም ስለ ኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መብት ለተደረገው ክርክር የጐጃምን ሊቃውንት ከወከሉት አንዱ ነበሩ። በዚህም የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የራሷን ሊቃነ ጳጳሳት እንድትሾም በተደረገው ትግል የመከራከሪያ አሳብ ከማመንጨት ጀምሮ ቀዳሚውን ቦታ ይዘው የሚገኙ ታላቅ የቤተ ክርስቲያን ሊቅ ናቸው። «በመንፈሳዊ ሕይወት ኀሥሮና ተግባር ወይም ለአንዱ የሚሰጥ

ለሌላው የሚነፈግ ክብር የሌለ በመሆኑ የኢትዮጵያ ሰዎች ከዐዋቂዎ ቻቸው ሊቃነ ጳጳሳት አይሹሙ ተብሎ በሥርዋጽ /በጣልቃ ገብነት/ በፍትሐ ነገሥት የተጻፈው ተሠርዞ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መብ ቷን ማግኘት አለባት» የሚል ነበር ያቀረቡት አሳብ:: ይኸንን አሳ ባቸውን በወቅቱ የደገፉቸው አልነበረም:: ተቃውሞ ብቻ ነበር የገጠ ማቸው:: ከጥቂት ጊዜያት በኋላ ሊቃውንቱ መከሩ:: ዐዋቂዎች በማስተዋል ተነጋገሩበት እናም ይኸን ታላቅ አሳብ ደገፉት:: ይኸው ዛሬ የእኒህ ታላቅ የቤተ ክርስቲያን ሊቅ አሳብ ፍሬ አፍርቶ የኢት ዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የራሷን ጳጳሳት፣ ሊቃነ ጳጳሳትና ፓትር ያርኮችን ለመሾም በቅታለች::

እኚህ የቤተ ክርስቲያን ሊቅ መልአከ ብርሃን አድማሱ ጀንበሬ ይባላሉ:: የተወለዱት ነሐሴ ፩ ቀን ፲፰፻፹፭ ዓ.ም በጐጃም ዲማ ጊ ዮርጊስ ነው:: ወላጆቻቸው አቶ ጀንበሬ አዲሱ እና ወ/ሮ ወለተ ማርያም ኃይሉ ይባላሉ:: እናታቸው ገና በአራስ ቤት እንዳሉ አንድ የእግዚአብሔር ሰው ወደ ቤታቸው መጣ:: እናም «ይህ ሕፃን እግዚ አብሔርን እንዲያገለግለው የመረጠው ነውና በጥንቃቄ አሳድጊው፤ በሰዓቱም ወደ ትምህርት ቤት አስገቢው» አላቸውና ሄደ:: እናታቸ ውም እንደተባሉት አደረጉ:: በዚህም የተነሣ የሕፃኑን ስም «ያለው» በማለት ሰየሙት:: «እግዚአብሔር ያለው ይሁን» ለማለት ነው:: አባታቸው ግን አድማሱ ይሏቸው ነበር:: ሆኖም ከትውልድ አገራቸው በአሥራ ዘጠኝ ዓመታቸው እስከ ወጡበት ፲፱፻፬ ዓ.ም ድረስ እና ታቸው ባወጡላቸው «ያለው» በሚባለው ስማቸው ነበር የተጠሩት:: ከዚያ በኋላ ግን አድማሱ የሚባለው ስማቸው ጎልቶ በሕይወት በነበ ሩበት ዘመን ሁሉ ሲጠሩበት ቆይተ ዋል::

ትምህርታቸውን የጀመሩት በተወለዱበት አገር ዲማ ጊዮርጊስ ነው:: አባ ወንድሙ የተባሉ ባሕታዊ ከፊደል ጀምሮ እስከ መዝሙረ ዳዊት አስተማሯቸው:: ቀጥሎ በፊት መሪጌታ በኋላ ሊቀ ጠበብት ክንፉ ከተባሉት አጎታቸው ዘንድ፤ ጾመ ድጓ፣ ምዕራፍ፣ ድጓ፣ ዝማሬ መዋሥዕትና ቅኔ ተማሩ:: ከዚያም በዲማ ቅዱስ ጊዮርጊስ በዲቁና፣





ማኅሌትና ስብሐተ ነግህ በመቆም እያገለገሉ በዚያው ካሉ ልዩ ልዩ ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን /መምህራን/ ቅኔና ትርጓሜ መጻሕፍትን ሲቀጽሉ ቆዩ::

ዕድሜያቸው ከፍ እያለ በአካል እየጠነከሩ በአእምሮ እየጎለመሱ መጡ:: የአርባዕቱ ወንጌላትን ንባብ ጽፈው በየዓመቱ ግንቦት ፲፪ ቀን የሚከበረውን የአቡነ ተክለ ሃይማኖትን በዓል ለማክበር በ፲፱፻፬ ዓ.ም ወደ ደብረ ሊባኖስ ገዳም መጡ:: ለመልአከ ብርሃን አድማሱ ይህ ለመጀመሪያ ጊዜ ከአገራቸው የወጡበት ነው:: በዚያ የጻፉትን መጽሐ ፍ ሸጠው ለስንቃቸው የሚሆናቸውን ገንዘብ ያዙና ወደ አዲስ አበባ አቀኑ::

አዲስ አበባ ገብተው ለጥቂት ቀናት የቆዩት በቅድስት ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ነው:: ከዚያም አካባቢ ከሚኖሩ ወልደ ሥላሴ ከሚባሉ የብ ሉይ መምህር ዘንድ ትርጓሜ ዳዊት፣ መጻሕፍተ ሰሎሞንና ትንቢተ ኢሳይያስን ሲቀጽሉ ቆይተው በግንቦት ወር ፲፱፻፰ ዓ.ም ተመልሰው ወደ ትውልድ አገራቸው ሄዱ:: ወደ አገራቸው እንደተመለሱ ትም ህርታቸውን በመቀጠል እዚያው ዲማ ከመምህር ወልደ ጊዮርጊስና ከመምህር እንግዳሸት ዘንድ ቅኔ እና ልዩ ልዩ መጻሕፍትን ቀጸሉ::

ትምህርታቸው በአካባቢያቸው ባሉት ሊቃውንት ብቻ እንዲወሰን አልፈለጉም:: በሌሎቹም የኢትዮጵያ ክፍላተ ሀገራት ካሉት ታላላቅ ሊቃውንተ ቤተ ክርስቲያን ዘንድ በመሔድ ትምህርታቸውን በመ ቅሰም ዕውቀታቸውን አሰፉ:: በፊት መሪጌታ በኋላ አለቃ ክፍሌ ደር ሰህ ከሚባሉ ዓይነ ሥውር ሊቅ ጋር በመሆን በ፲፱፻፯ ዓ.ም ወደ ደሴ ሄዱ:: ደሴ ከመልአከ ገነት አፈ ወርቅ ፍትሐ ነገሥትን እንዲሁም ከመምህር አካለ ወልድ ቦሩ ሜዳ /የቀለም ቀንድ/ ዘንድ አዲሳትንና መጻሕፍተ ሊቃውንትን ተማሩ::

በዚያን ጊዜ መሳፍንትና መኳንንቱ የነገሥታቱንና የአባቶቻቸውን ሥርዓት በመከተል ሊቃውንቱን እየፈለጉ በዐቢይ ጾም የዳዊትን፣ በሰ ሙነ ሕማማት የመጻሕፍተ ኪዳንን፣ በጾም ፍልሰታ የውዳሴ ማርያ ምንና የቅዳሴ ማርያምን ትርጓሜዎች ይሰሙ ነበር:: መልአከ ብርሃን

አድማሱም ውዳሴ ማርያምንና ቅዳሴ ማርያምን ትርጓሜ በጾመ ፍልሰታ ለራስ ሀብተ ማርያም ለማሰማት ተመርጠው ሄዱ:: ራስ ሀብተ ማርያምም ትዕግሥታቸውን፥ ትኅትናውንና ችሎታቸውን በማየት ሙያና ባለሙያ እንዲህ ሲገኝ እጅግ መልካም ነው በማለት ያደንቋቸው ነበር:: ራስ ሀብተ ማርያም በበገና መጸለይ ይወዱ ነበር:: የበገና መዝሙር እንዲያዘጋጁላቸውም መልአከ ብርሃን አደማሱን ጠየቋቸው:: እርሳቸውም የመጀመሪያቸው የሆነውን «የበገና መዝሙር» የተባለ መጽሐፍ ከቅዱሳት መጻሕፍት አውጣጥተው ማዘጋጀት ጀመሩ:: በኋላ ይኸንኑ መጽሐፍ በማስተካከልና በመረጃ ማነጻጸሪያነት የተጠቀሙባቸውን መጻሕፍት ጠቅሰው አስፋፍተው በ፲፱፻፳፯ ዓ.ም አሳትመውታል::

መልአከ ብርሃን አድማሱ በ፲፱፻፱ ዓ.ም ደሴ የመጡበትን ትምህርት ሲያጠናቅቁ ወደ ጎጃም ተመልሰው ከብሉይ ሊቅ አለቃ ገብረ ኤልያስና ከቅኔው ሊቅ ከመልአከ ሰላም ገብረ ማርያም ደንበጫ ብሉያትን ሲቀጽሉ ቅኔውን ሲያስፋፉ ዕውቀታቸውን ሲያሰፉ እስከ ፲፱፻፲፰ ዓ.ም ድረስ ቆዩ:: ከዚያም ወደ ዲማ መጥተው የቅኔ መምህር በመሆን እስከ ፲፱፻፳፬ ዓ.ም ድረስ ሲያስተምሩ ቆይተዋል:: በዚህ ጊዜ መተዳደሪያቸው ልዩ ልዩ መጻሕፍትን በቁም ጽሕፈት፣ በብራና እየጻፉ በመሸጥ ነበር:: እንደ ልጃቸው አቶ ምኅርካ ክርስቶስ አድማሱ ገለጻ ከልጆቻቸው እናት ከወ/ሮ ዓለሚቱ አሸቴ ጋር ትዳር የመሠረቱት በ፲፱፻፲፰ ዓ.ም አካባቢ ነው::

በ፲፱፻፳፭ ዓ.ም ወደ አዲስ አበባ መጡ:: በዚያን ጊዜ የመጽሐፈ ግጻዌን ረቂቅ አዘጋጅተው ቀሌምንጦስና መጽሐፈ ኪዳን የተባሉትን መጻሕፍት በብራና ጽፈው መጥተው ነበርና ሁለቱንም መጻሕፍት ብፁዕ አቡነ አብርሃም ገዝተዋቸው ለመንበረ መንግሥት ቅዱስ ገብርኤል ሰጥተው በዚያ ይገኛሉ:: የግጻዌውን ረቂቅ ለቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ አቅርበው ንጉሡም በሊቃውንት ተመርምሮ እንዲታተም እርሳቸውም በቁም ጽሕፈት ቤት እንዲሠሩ አዘዙ:: ይህ መጽሐፈ ግጻዌ በሊቃውንቱ ተመርምሮ ለኅትመት ከቀረበ በኋላ የኢጣሊያ ወረራ





ሥራውን ሁሉ ስለ አሰናከለው ቆይቶ በ፲፱፻፵፭ ዓ.ም ታትሟል:: ከፋሺስት ጣሊያን ወረራ በኋላ መጽሐፉ እንዲታተም ንጉሡ ለመልአከ ብርሃን አድማሱ የጻፉላቸው ደብዳቤ እንዲህ ይላል::

*ሞዓ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ*
*ሥዩመ እግዚአብሔር ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ*
*ለመልአከ ብርሃን አድማሱ*

*እንደምን ሰንብተሃል እኛ በእግዚአብሔር ቸርነት ደኅና ነን:: የጻፍክልን ደብዳቤ ደርሶናል:: የጻፍከውን መጽሐፍ ካየነው በኋላ እንዲታተም በፍጥነት ይዘኸው እንድትመጣ ይሁን:: /መጋቢት ፲፯ ቀን ፲፱፻፴፭ ዓ.ም አዲስ አበባ::/*

የዳግማዊ ምኒልክ መታሰቢያ ትምህርት ቤት ሲከፈት በሊቀ ሊቃውንት ገብረ አብ በኋላ አቡነ ፊልጶስ አማካይነት ከተመረጡት ሊቃውንት አንዱ በመሆን መጋቤ ምሥጢር አድማሱ ተብለው ተሹመዋል:: ይህ መዓርግ ለእሳቸው የመጀመሪያቸው ሲሆን ሹመቱም ገና አዲስ ለመጀመሪያ ጊዜ የተሰጠ ነበር:: ይህ ሹመት በእንደዚህ ዓይነት አስተዋይ፣ ተመራማሪ፣ ሥራ ወዳድና ሁልጊዜም ተማሪ በሆኑ ሰው መሟሸቱ ከተሿሚው ይልቅ ሹመቱ ዕድለኛ ነበር ይባላል::

በ፲፱፻፳፯ ዓ.ም በጐጃም ጠቅላይ ግዛት ብቸና ቅዱስ ጊዮርጊስ ሊቀ ጠበብትነት በንጉሠ ነገሥቱ መልካም ፈቃድ ስለ ተሰጣቸው ሊቀ ጠበብት አድማሱ ተብለው ወደ አገራቸው ተመለሱ:: ከ፲፱፻፳፰ ዓ.ም የፋሺስት ኢጣሊያ ወረራ ጊዜ ጀምሮ እስከ ሚያዚያ ወር ፲፱፻፴፫ ዓ.ም ጣሊያን ተሸንፎ ከኢትዮጵያ እስከ ወጣበት ጊዜ ድረስ በኃዘንና በጸሎት ተወስነው ቅኔ እያስተማሩ እንዲሁም ዲማ ጊዮርጊስ ለተቋቋመው የጀግኖች ማኅበር አባል ሆነው የአርበኝነቱን ሥራ እየሠሩ ቆይተዋል:: ለዚሁም አገልግሎታቸው ከድል በኋላ ባለ ሦስት ዘንባባ ሜዳይ ከንጉሠ ነገሥቱ እጅ ተሸልመዋል::

በ፲፱፻፴፫ ዓ.ም በብቸና ቅዱስ ጊዮርጊስ ራስ ወርቅ አሠረው መልአከ ብርሃን ተብለው ተሾሙ:: ይህን እንጂ ከዚህ ጊዜ ጀምሮ በጠቅላይ ቤተ ክህነት ተፈላጊነታቸው እየበዛ ስለሄደ ለተሾሙበት አገር ለብቸና እንደ ራሴ ሰጥተው በአዲስ አበባ በጠቅላይ ቤተ ክህነት ሲሠሩ ኖረዋል::

መልአከ ብርሃን አድማሱ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስተያን ከራሷ
የቤተ ክርስቲያን አባቶችና ሊቃውንት መነኰሳት መካከል ሊቃነ ጳጳ
ሳት ልትሾም ይገባታል፤ መብቷን ማግኘት አለባት፤ የሚለውን አሳብ
አቅርበው መከራከራቸው ይታወቃል።

ከዚያም ወዲህ ለቤተ ክህነት አስተዳደር መንፈሳዊ ጉባኤ ሲቋቋም
ለአስተዳደር ከተመረጡት የመማክርት አባላት አንዱ ሆነው አገልግ
ለዋል። ቀጥሎም የቤተ ክርስቲያን አስተዳደር የሚመራው በመማክ
ርት መንፈሳዊ ጉባኤ መሆኑ ቀርቶ በሊቀ ብርሃን አድማሱ የታሪክና
ድርሰት ክፍል ሹም፣ የሊቃውንት ጉባኤ ፕሬዝዳንት በመሆን አገልግ
ለዋል። መልአከ ብርሃን አድማሱ በሥራቸው ላይ ብቻ የሚወሰኑ አልነ
በሩም። በተፈጥሮአቸው መወያየትን፣ መመራመርን፣ መጠየቅን፣ ሲጠ
የቁም በሚገባ ማስረዳትን የሚወዱ ናቸው። ማናቸውንም ዓይነት መ
ጽሐፍ ያነብባሉ። ብዙ መዝናናትና ዕረፍት አይሹም ትርፍ ጊዜ
የሚባል የላቸውም። ከሥራ ሰዓት ውጪ ያላቸው የጸሎት ጊዜ፣ ቤተ
ክርስቲያን የሚሄዱበት የሚያስቀድሱበት ወይም የሚያገለግሉበት ጊዜ
ነው። ከዚህ ወጪ በሚያገኙት ጊዜ ሁሉ ያነብባሉ፤ ይጽፋሉ። በዚህ ጊ
ዜና ሁኔታ ነው «ኰኲሐ ሃይማኖት» የተባለውን የመልስ መጽሐፍ ያሳ
ተሙት።

በ፲፱፻፵፱ ዓ.ም በንጉሠ ነገሥቱ የከፍተኛው ፍርድ ቤት ዳኛ
ሆነው ተሾሙ። በዚህም የመንግሥት ሓላፊነታቸው ወቅት በበጌምድ
ርና በሰሜን፣ በወሎ፣ በትግሬ ጠቅላይ ግዛቶች ተዘዋውረው ብዙ የፍ
ርድ ጉዳዮችን ፈጽመዋል። በፍርድ ምርመራ ተመድበው ለብዙዎች
አስቸጋሪ የነበሩ ጉዳዮች መፍትሔ እንዲገኝላቸው ማድረጋቸው በብ
ዙዎች ዘንድ ተመስክሯል። በፍርድ ቤት ሲሠሩ በነበሩበት ወቅት
የቤተ ክርስቲያን አገልግሎታቸውን አልቀነሱም። ከመንግሥታዊ የፍ
ትሕ ሥራቸውና የቤተ ክርስቲያን አገልግሎታቸው ውጪ ጊዜያቸውን
በሚገባ ይጠቀሙበት ነበር።

መልአከ ብርሃን አድማሱ በልዩ ልዩ ድርጅቶች፣ በትምህርት
ቤቶች፣ በኢትዮጵያ ሬድዮና በብሥራተ ወንጌል ሬዲዮ ጣቢያዎች





እየተገኙ መንፈሳዊ ትምህርት ይሰጡ ነበር። እንዲሁም ከልዩ ልዩ አቅ
ጣጫ ለሚቀርቡላቸው፤ ሕግና ፍልስፍና፣ እምነትና ምግባር፣ ታሪክ፣
ባህልና ቋንቋ ጠቀስ ለሆኑ ጥያቄዎችም መልስ መስጠት ዋና ተግባራ
ቸው ነበር። «መድሎተ አሚን» የተባለውን መልስ ሰጪ መጽሐፋቸ
ውንም አዘጋጅተው ያሳተሙት በዚሁ ጊዜ ነው።

ከፍርድ ሚኒስቴር የፍርድ ሥራቸው በ፲፱፻፶፱ ዓ.ም በጡረታ ሲ
ገለሉ ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን አለኝታ ስለነበሩ እንደገና በጠቅላይ
ቤተ ክህነት መጻሕፍትን እንዲተረጉሙ፣ እንዲመረምሩና በጠቅላላ
በቤተ ክርስቲያን ዐበይት ጉዳዮች ወይም እንቅስቃሴ ላይ ተካፋይ እን
ዲሆኑ ተደረገ። ይህም ጊዜ ከሃያ ዓመታት በላይ ከየቦታውና ከተለያዩ
ሰዎች እየሰበሰቡ በማጠራቀም የደከሙበትን «ዝክረ ሊቃውንት» የተባ
ለውን የሀገራችንን ሊቃውንት /ባለ ቅኔዎች/ ታሪክ የሚያስረዳ መጽሐ
ፍ አዘጋጅቶ ለኅትመት ለማብቃት ምቹ ጊዜ ሆነላቸው። /መጽሐፉን
ለኅትመት አዘጋጅተው እርሳቸው ስላረፉ የታተመው ጥቅምት ፩ ቀን
፲፱፻፷፫ ዓ.ም ነው/።

መልአከ ብርሃን ዋናው ሥራቸው በቤተ ክህነት ነበር ቢባልም አን
ዳንድ ድርጅቶች ስለ ኢትዮጵያ ባህልና ታሪክ ለሚያደርጉት ጥናትና
ምርምር የሞያ ድጋፍ ያደርጉላቸው ነበር። ከእነዚህም ውስጥ «የኢትዮ
ጵያ የጥንት ቅርስ ጥበቃ ድርጅት» ባደረገው እንቅስቃሴ በመሳተፍ
በጐጃም ጠቅላይ ግዛት በተለያዩ አድባራትና ገዳማት ያሉትን መጻሕ
ፍትና ልዩ ልዩ ቅርሳ ቅርስ ዝርዝር በድርጅቱ ከታሰበው በላይ በተ
ሟላ ሁኔታ አዘጋጅተው አቅርበዋል። የዚህ ዝርዝር ሥራቸው ቅጅ
በወቅቱ በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዩኒቨርስቲ የኢትዮጵያ ጥናት ክፍል
ይባል በነበረው ይገኛል። እንዲሁም የትምህርትና ሥነ ጥበብ ሚኒስ
ቴር በየቤተ ክርስቲያኑ የሚገኙትን መጻሕፍት በማይክሮ ፊልም ለማ
ንሣት ባደረገው ጥረት በጎጃም ጠቅላይ ግዛት ብቸና አውራጃ የሚገ
ኙትን ምርጥና ጥንታውያን መጻሕፍት በማዘጋጀት በድርጅቱ ሥራ
ተካፋይ ሆነዋል።

በዕረፍት ጊዜያቸው የሃይማኖት መጻሕፍትን መመርመር፣ የታሪ
ክና ልቦለድ መጻሕፍትን ማንበብ፣ ስለ ሃይማኖት ለጠያቂዎች

ማስረዳት ዋና ተግባራቸው እንደሆነ አድርገው ይሠሩበት ነበር፡፡ እንደ
ምሳሌ በኢትዮጵያ ሬዲዮና በብሥራተ ወንጌል ሬዲዮ ጣቢያዎች በየጊ
ዜው ያስተላለፉትን ትምህርት ማስታወስ በቂ ነው፡፡ «ሐዲስ ሰውነት»
የተባለው መጽሐፋቸውም በዐቢይ ጾም ጊዜ በኢትዮጵያ ሬዲዮ የሰጡ
ት ተከታታይ ትምህርት ነው፡፡ መልአከ ብርሃን አድማሱ መጻሕፍትን
ዝም ብሎ ከመቀበል ይልቅ አስቀድሞ በጥልቀት መመራመርን ይወዱ
ነበር፡፡ ከመጻሕፍት ውስጥ አልፎ አልፎ በሚገባ ያልተብራሩና ትር
ጉም ያልተሰጣቸው አነጋገሮች ሲያጋጥሙ በቂ የሆነ ትርጉም ይሰጡ
ነበር፡፡ ታላቁ ሊቅ አለቃ ኀሩይ ፈንታም መልአከ ብርሃን እንደተረ
ጐመው» እያለ ያስተምሩ እንደነበር የጉባኤው ተካፋይ የነበሩት ሁሉ
ምስክሮች ናቸው፡፡ መልአከ ብርሃን አድማሱ እስከ ዕድሜያቸው መጨ
ረሻ ድረስ በአካለ ሥጋ እያሉ ዕረፍት አልነበራቸውም፡፡ ለዚህ ምስክሩ
ከፍተኛ ትኩረት ይሰጡት የነበረውን «ዝክረ ሊቃውንት» የተባለው
መጽሐፋቸው ከፍጻሜ ደርሶ ለማየት በጣም ይጓጉ ነበር፡፡ በዚሁ ሥራ
ቀን ከሌሊት ይተጉ ነበር፡፡ ይህንኑ መጽሐፍ አዘጋጅተው በማሳተም
ላይ ሳለ ሥራውን ሳይጨርሱት ቀን ሲሠሩ ውለው ማታ በደረሰባቸው
ድንገተኛ ሕመም የአእምሮ ድካም /ስትሮክ/ ሐምሌ ፳፬ ቀን ፲፱፻፷፱
ዓ.ም ዐረፉ፡፡ የቀብራቸውም ሥነ ሥርዓት ብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት ሊቃ
ውንተ ቤተ ክርስቲያን ካህናትና ወዳጅ ዘመዶቻቸው በተገኙበት በቅ
ድስት ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ተፈጽሟል፡፡ መልከ ብርሃን አድማሱ
ጀንበሬ ከባለቤታቸው ከወ/ሮ ዓለሚቱ እሸቴ ሰባት ልጆች አፍርተዋል፡፡

በቅርብ ያውቋቸው የነበሩ እንደሚናገሩትና በተለያዩ ጊዜያት ስለ
እርሳቸው የጻፉ ጽሑፎች እንደሚገልጹት፤ መልአከ ብርሃን አድማሱ
ጀምበሬ ተግባረ ዕድን በጣም የሚወዱ በሌላው ጉልበት በከንቱ ሊጠ
ቀሙ የማይፈቅዱ ታላቅ ሰው ነበሩ፡፡ በብዙ ጊዜ ሥራቸው ጽሕፈት
ስለሆነ በተለያዩ ጊዜያት ሰማንያ አንድን ቅዱሳት መጻሕፍትን በእጃ
ቸው ጽፈው ጨርሰዋል፡፡ «በድካሜ ፍሬ እንድረዳ በማድረጉ ፈጣሪዬን
አመስግነዋለሁ» ይሉ ነበር፡፡

መልአከ ብርሃን አድማሱን በተመለከተ ተጽፈው የታተሙ ጽሑ
ፎች እንደሚገልጹት መልአከ ብርሃን ጠባያቸው ትዕግሥትን የተሞላ





ነበር፡፡ ይኸውም በአንድ መልክ ብቻ የተወሰነ አልነበረም፡፡ እኔ ልክ
በር፣ እኔ ልመስገን፣ እኔ ልናገር፣ እኔ ልቅደም፣ እኔ ልታወቀ፣ እኔ
ሙሉ ችሎታና ብቃት አለኝ ማለት በእሳቸው ዘንድ በፍጹም አልነ
በረም፡፡ አይታወቅም፡፡ መልአከ ብርሃን አድማሱ መጻሕፍትን በሙሉ
መልካቸው ያውቋቸው ስለነበር በንባባቸውም ሆነ በትርጓሜያቸው
ተጠይቀው ለመመለስ እና አጥጋቢ ትምህርት ለመስጠት የሚቻላቸው
ሰው ነበሩ፡፡ እንኳን በቁም ነገሩ ጊዜ በጨዋታው ጊዜም ቢሆን ትም
ህርታዊነት የሌለው ቃል ከአንደበታቸው አይወጣም፡፡

አርቆ ማስተዋል፣ ጠልቆ መመርመር፣ ለመናገር አለመቸኮል፣
አስተውሎ መናገር፣ እውነትን መድፈር፣ የሰውን ክብር መጠበቅ፣ ሰውና
እግዚአብሔርን አጣምሮ መውደድ፣ ሰው ደስ እንዲለው መጣር፣ እግ
ዚአብሔርን መፍራት፣ ሀገርን መውደድ፣ ሰውን አለማሳዘን፣ የሥራ
ጊዜን አለማባከን፣ በሥራ አለመለገም፣ ምላስንና ልቡናን መግዛት፣ ሲ
ችሉ እችላለሁ አለማለት፣ መጻሕፍትን የሁልጊዜ ጓደኛ ማድረግ፣
ዓይንንም ልብንም እጅንም ከሥራ አለመለየት፣ ጽኑ ሃይማኖትና ፍጹም
ትዕግሥት መልአከ ብርሃን አድማሱ የሚታወቁባቸው ጠባያት ነበሩ፡፡

መልአከ ብርሃን አድማሱ በትርጓሜ መጻሕፍት ቃል በቃል የተቀ
በሉትን ብቻ ሳይሆን እየመረመሩ እያስተዋሉ የሚያዳብሩ፤ የጐደለ
ውን እየሞሉ የጠመመውን እያቀኑ ያስተምሩ ስለነበረ ትርጓሜያቸው
ሁሉ ጣዕምና ምሥጢር የተካከሉት ነበር፡፡

ዕውቀታቸው በእምነት ላይ የተመሠረተ ነበረ፡፡ አንድ ጊዜ
ልጃቸው በጠና ታሞ ለሞት ይደርሳል፡፡ ቤተሰብ ወዳጅ ዘመድ ልቅሶ
ጀመረ፡፡ ተሰብስበው የነበሩት ሰዎች የሕፃኑን አስከሬን ወደ መቃብር
ለመውሰድ መግነዙን አሰናድተው ሲመጡ መልአከ ብርሃን አድማሱ ሕፃ
ኑን አቅፈው ሲጸልዩ አገኟቸው፡፡ ሰዎቹ የሕፃኑን መሞት ባለማወቅ
የሚያደርጉ መስሏቸው ያጉረመርሙ ነበር፡፡ እሳቸው ግን «ትላንትና
በሥጋ ተገልጦ የሰዎችን ልመና ስትቀበል፣ ድውያንን ስትፈውስ፣
ሙታኖቻቸውን ስታስነሣ የነበርክ አንተ ነህ፡፡ ዛሬም የአለህ አንተ ነህ፡፡
አልተለወጥክም፡፡ እኔም ከእነዚያ ባላነሰ እምነት አምንሃለሁ፡፡ አሁንም

«አዝዝ በቃልከ ይሕየው ወልድየ፤ ልጄ እንዲድን በቃል እዘዝ፤» እያሉ
ይጸልዩ ነበር:: ብዙ አልቆየም:: ጸሎታቸው ተሰማ:: እግዚአብሔር
ልመናቸውን ተቀብሎ በእቅፋቸው ላይ እንዳለ የሕፃኑ ነፍስ ተመ
ለሰች:: ዓይኑንም ገልጦ ይመለከት ጀመር:: የቤተሰቡም ሀዘን ወደ
ደስታ ተመለሰ:: በአካባቢው የተሰበሰበው ሕዝብ ሁሉ የእስልምና እም
ነት ተከታዮችም ሳይቀሩ የእምነታቸውን ጽናት ተረዱት:: ይህ ሕፃን
አድጎ ዛሬ አንቱ የተባለ ትልቅ ሰው ሆኗል:: እኝሁ ልጃቸው አገራች
ውንና ወገናቸውን በተማሩ የአካውንቲንግ ሞያ ለረጅም ዘመናት
በማገልገል ላይ ይገኛሉ::

### ስለ መልአከ ብርሃን አድማሱ ጀንበሬ<br>የሰዎች ምስክርነት

«መልአከ ብርሃን አድማሱ ጀንበሬን የማውቃቸው ሲነገር ከምሰ
ማው ሥራቸውና የጻፏቸውን መጻሕፍት አንብቤ ነው:: ደብረ ሊባኖስ
ገዳም በነበርኩበት ጊዜ እሳቸው በስተእርጅና ዕድሜያቸው ሲመጡ
ለጥቂት ቀናት አይቻቸዋለሁ:: ከባለ ቤታቸው ከወ/ሮ ዓለሚቱ እሸቴ
/በኋላ እማሆይ ዓለሚቱ/ ጋር ግን በተለያየ ጊዜ ደብረ ሊባኖስ እየ
መጡ በጣም እንግባባ ነበር::

በአንድ ወቅት እማሆይ ዓለሚቱ ከወንድማቸው ጋር ደብረ ሊባኖስ
መጥተው ለስድስት ወራት ያህል ቆይተው ነበር:: በዚያን ወቅት
እማሆይ ዓለሚቱ ስለልጃቸው ሲያጫውቱኝ ልጃቸው በሕፃንነቱ ታሞ
በሞት ጊዜ ቤተዘመድ ሁሉ ሲያለቅስ ከእግዚአብሔር ጋር የምነጋገ
ረው አለኝ ብለው ሰውን ሁሉ አስወጡ:: እንባቸው በልጁ አስከሬን
ላይ እየተንጠባጠበ ይጸልዩ ነበር:: እኔ አእምሮአቸው የተዛባ መስሎኝ
እባካችሁ አስጥሉ እያልኩ እናገር ነበር:: በኋላ ልጁ ዓይኑን ገልጦ
ተነሣ:: ልጁን በጸሎታቸው «አዝዝ በቃልከ ይሕየው ወልድየ» እያሉ
ከሞት አሥነሥተው እግዚአብሔርን እየመሰገኑ ሰጡኝ» በማለት አጫ
ውተውኛል::

መልአከ ብርሃን አድማሱ ጀንበሬ ከሊቅነት ጋር ሃይማኖት ያላ
ቸው የጸሎት ሰው ነበሩ:: ታላቅ ምሁር ናቸው:: ጠንካራ እምነት
ነበራቸው::»

*ብፁዕ አቡነ ቶማስ*<br>*የአዊና የመተከል አህጉረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ*





«ከመልአከ ብርሃን አድማሱ ጀንበሬ ጋር የመተዋወቅ ብቻ ሳይሆን
አንድ ቤተሰብ ነን:: ከ፲፱፻፴ ዓ.ም ጀምሮ አውቃቸዋለሁ:: የተወ
ለዱትና ያደጉት አገራቸው ምሥራቅ ጐጃም ብቸና አውራጃ ዲማ ጊዮ
ርጊስ ነው:: ወላጆቻቸው አቶ ጀንበሬ አዲሱ እና ወ/ሮ ወለተማርያም
ኃይሉ ይባላሉ:: ደግ ቤተሰቦች ናቸው:: የእግዚአብሔር ሰዎች ነበሩ::

መልአከ ብርሃን ገና በእናታቸው ጀርባ እያሉ አንድ ባሕታዊ
መጥቶ «ይሄ ያዘልሽው ልጅ ቤተ ክርስቲያን የሚጠቅም ነው» ብሎ
እንደነገራቸው ይነገራል:: እናታቸውም <እግዚአብሔር ያለው አይ
ቀር> ብለው ስማቸውን <ያለው> አሏቸው:: አባታቸው ደግሞ አድማሱ
አሏቸው:: በዚያ ምክንያት ብዙ ጊዜ በትውልድ አገራቸው አካባቢ
<ያለው> ነበር የሚባሉት:: አድማሱ የሚለው ስም በኋላ ነው ገኖ ያደገው::

መልአከ ብርሃን ተወልደው ያደጉበት ዲማ ለሥጋዊ ምቾት ያን
ሰው ይሆናል እንጂ በመንፈሳዊው በኩል ዲማ የተፈለገው ምሁር ሁሉ
በየመልኩ ይገኛል:: ከንባብ ጀምሮ እስከ ትርጓሜ መጽሐፍ የተፈለገው
መምህር ሁሉ የሚገኝበት መንፈሳዊ አገር ነው:: እዚያ ለተወለዱት
ብቻ ሳይሆን ከውጪ ለመጡትም ቢሆን በየዓይነቱ ትልቅ ልግስና
አለው:: ታቦቱ ረድኤት አለው:: እዚያ ደጅ የጠና ሁሉ ያገለገለ ሁሉ
አያፍርምና ከዚህ ዕድል ውስጥ ነው እንግዲህ መልአከ ብርሃን ያን
መንፈሳዊ ሀብት ይዘው ያደጉት:: ከልጅነታቸው ጀምሮ በዲቁናም፣
በመዘምርነትም፣ በቅኔውም፣ በመምህርነትም እግዚአብሔ ርን እዚያ
አገልግለዋል:: ትምህርታቸውም እዚያው ከአባቶቻቸው ያገኙት እንጂ
ከውጪ አልሄዱም::

ከዚያ በኋላ ብዙ ጊዜ ከተማ ኖረዋል:: መጀመሪያ ደሴ ንጉሥ
ሚካኤል ግቢ ከዚያም ደግሞ ወደ አዲስ አበባ መጥተው መጋቤ ምሥ
ጢር ተብለው በኣታ ለማርያም ገዳም አገልግለዋል:: እንደውም ይህ
ንን ሹመት አስመልክቶ ሹመቱ እድለኛ ነው:: በእሳቸው ተጀመረ
ይባል ነበር:: የመጀመሪያው መጋቤ ምሥጢር እሳቸው ናቸው:: አዲስ
አበባ በበኣታ ለማርያም ገዳም አራቱ ጉባኤያት ሲሠየም ቅኔ መምህ
ርነቱም የተጀመረው በእሳቸው ነው:: ከጠባያቸው ሙያቸው

ከሙያቸው ጠባያቸው ይኸ ይነቀፋል የሚባል ነገር የለባቸውም:: የሚያስደንቀው ነገር ይሄ ነው:: ቁጣ አያውቁም ከሰው ጋር ሲነጋገሩ በትኅትና በአክብሮት ነው እንጂ ቁጣ የለባቸውም:: ተጠይቀው ደግሞ የሚያስረዱት አያጡም:: ለተጠየቁት ጥያቄ ሁሉ መልስ አይቸግራቸውም:: ሙሉ ሰው ናቸው::

እኔ በ፲፱፻፴ ዓ.ም በጠላት ዘመን አለቃ ማርቆስ ከሚባሉ መምህር ዘንድ ቅኔ ቤት ነበርኩኝ:: በዚያን ጊዜም ሆነ ከዚያ በኋላ እያደግሁ ስመጣም ብዙ ጊዜ ጥያቄ የምጠይቀው መልአከ ብርሃንን ነው:: እሳቸውም በሚገባ ያስረዱኝና ይከታተሉኝ ነበር:: በዚያን ጊዜ የነበረው የዓይነ ሥውሮች ሕይወት ከቤተ ክርስቲያን ከተረፈ ልመና ነው:: የቤተ ክርስቲያን ጥገኛ ሆኖ መኖር ነው:: መልአከ ብርሃን ከቤተ ክርስቲያን እንዳልርቅ ብዙ ጊዜ ይቆጣጠሩኝ ነበር:: ይሄ በመሆኑ እንደ አባቴ ነው የማያቸው:: በተለይ ለእኔ እዚህ መድረስ የመልአከ ብርሃን አድማሱ ትልቅ አስተዋጽኦ አለው ማለት ነው::

ጣልያን ከአገር ከወጣ በኋላ በ፲፱፻፴፱ ዓ.ም አካባቢ ወደ አዲስ አበባ መጥተው ሊቀ ጠበብት ተብለው ነበር:: በኋላ ጎጃም ምሥራቅ ብቸና ጊዮርጊስ መልአከ ብርሃን ተባሉ:: በዚህ ምክንያት እየተመላለሱ ሁለቱም ጋ ነበር የሚሠሩት:: ብቸናን በእንደራሴ እያስተዳደሩ አዲስ አበባ ጠቅላይ ቤተ ክህነት የመንፈሳዊ ጉባኤ አባል ነበሩ:: ይህ ጉባኤ ሰባ ሊቃውንት የነበሩበት ከፍተኛ የቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ አስተዳደር ጉባኤ ነበር:: ይኸ በመሆኑ መልአከ ብርሃንም እየተመላለሱ ይሠሩ ነበር::

ስለ ኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መብት ራሷን እንድትችል የተደረገውን ክርክር በተመለከተም መልአከ ብርሃን አድማሱ ይጠቀሳሉ:: የግብጹ ጳጳስ አቡነ ቄርሎስ በጣሊያን ጊዜ ጥለው ወደ ግብጽ ሄደው ነበር:: ከነፃነት በኋላ እንደገና ተመልሰው እንዲመጡ ተደረገ:: ተመልሰው ሲመጡ ሊቃውንቱ አንቀበልም አሉ:: ጠብ ተነሣ:: በዚህ ምክንያት ከዚህ በኋላ እንለያያለን የሚል ነገር መጣ:: ሊቃውንቱ ለሁለት ተከፈሉ:: ከሁለት ሲከፈል ግማሾቹ እንደቀድሞው በግብጽ ጳጳስ





ይመራ የተቀረው ደግሞ አይሆንም አሉ:: የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ራሷን መቻል አለባት የሚል አሳብ መጣ:: በዚህ ጊዜ በፍትሐ ነገሥት የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ከዐዋቂዎቻቸው እንዳይሾሙ ተከልክሏል የሚል ነገር መጣ:: ይኸ በሥርዋጽ የገባ ነው እንጂ ዋና ቃል አይደለም:: በክርስትና የበላይና የበታች ገዥና ተገዥ የለም:: ምንም የሚከለክል ነገር የለም ነው የሚለው:: ለካ ያን ጊዜ መልአከ ብርሃን አድማሱ ይሄንን ሃሳብ አቅርበው ነበር:: ክርክሩም ቀጥሎ መጀመሪያ ታፈሠ ሃብቴ የሚባሉ በኋላም መልአከ ብርሃን አድማሱ ጀንበሬ፣ አሥራት ካሣ፣ አቡነ ቴዎፍሎስ፣ አቡነ ዮሐንስ፣ ያሉበት ጉባኤ ተፈጥሮ ጉዳዩ በክርክር ከቆየ በኋላ ተፈቀደ:: ኢትዮጵያ ራሷን እንድትችል ሹመቱ ግን ከግብጽ ሆኖ በኢትዮጵያ ሊቀ ጳጳሳት እንድትመራ የሚል ነበር::

ከመልአከ ብርሃን ጋር አዲስ አበባ ከመጣሁም በኋላ አልተለያየንም:: የአንድ አያት ልጆች ሆነን የስጋ ዝምድና ቢኖረንም ከእሳቸው አልለይም ነበር:: ጠባያቸው ትዕግሥትን የተሞላ ነበር:: ትዕግሥታቸው በአንድ አቅጣጫ የተወሰነ ብቻ አልነበረም:: በሁሉም ዘንድ በሁሉም አቅጣጫ ነው:: መልአከ ብርሃን ቁጣ አይወዱም በጣም ነፃ ሰው ናቸው:: ደግነት አላቸው:: ሆኖ ከተገኘ እሳቸው ጋር የሚነቀፍ የለም:: ሆኖ መገኘት ብቻ ነው:: ካልሆነ ደግሞ መቀበልም የለም:: ሆኖ ከተገኘ ደግሞ ልጅ ነው አዋቂ ነው፣ ድሃ ነው ሃብታም ነው፣ ባለ ሥልጣን ነው ተራ ሰው ነው በእርሳቸው ዘንድ ምንም ልዩነት የለም::

በተለይ ለእኔ እንደአባቴም እንደ መምህሬም ነበሩ:: ያልገባኝን ነገር ሁሉ የምጠይቀው እሳቸውን ነው:: ያን ጊዜ ታዲያ ሀገር የጋራ ነው ሃይማኖት የግል ነው ተብሎ ስለታወጀ ሚሲዮናውያንም ካቶሊካውያኑም ገቡ:: የካቶሊክ መንበር ተዘረጋ:: የፕሮቴስታንት ቤተ ክርስቲያን ተከፈተ:: የእስላም መስጊድ በያለበት ተከፈተ:: ያ ሁሉ እየደገ ሲመጣ የሃይማኖት ውዥንብር ነበር:: በዚህ ምክንያት ብዙ ጥያቄዎች ይነሡ ነበር:: እኔም በወቅቱ ከመምህር ፈላታዎስ ዘንድ ብሆንም በዘመኑ የነበሩኝን ጥያቄዎች ሁሉ መልአከ ብርሃን ጋር እየሄድኩ ነበር

የማጣራው:: በኋላም መምህር ፊላታዎስ ወደ ሃገራቸው ሄደው እዚ ያው ዐረፉ:: እንግዲህ በጠቅላላው አሳቤ ወደ እርሳቸው ተመለሰ:: በዚህ ምክንያት ከእሳቸው ጋር ነው የምውለው የምጠይቀውም:: መድሎተ አሚን፣ ኰኵሐ ሃይማኖት መጻሕፍታቸውን ሲያዘጋጁ ሁሉ አብሬያ ቸው ነበርኩ::

መልአከ ብርሃን ካዘጋጇቸው መጻሕፍት በሁሉም ይሄ ከዚህ ይሆናል ይሄ ይቀንሳል የሚል የለኝም:: መጻሕፍቱ ሁሉ የሚነቀስ እን ከን የላቸውም:: ከትውልድ ትውልድ እየተላለፉ የሚያገለግሉ የሚያስ ተምሩ መጻሕፍትን ነው አዘጋጅተው ያረፉት::

መልአከ ብርሃን ከጉያቸው መጽሐፍ አይለይም:: ሲበሉም በአንድ እጃቸው መጽሐፍ ይዘው ነው:: መጽሐፍ አስቀምጠው አይበሉም:: <ኧ ረ እባክዎ ዓይንዎ ይደክማል ይጐዳል> ሲሏቸው «የተፈጠረው ለዚህ ብሎ ነው:: ለዚህ ካላገለገለ ይፍረጥ እንጂ እኔ ምን አደርገዋለሁ» ይሉ ነበር:: በመጨረሻም ሊቃውንቱ እያለቁ በመሄዳቸው ታሪክም እየጠፋ ስለሄደ የሊቃውንቱን ታሪክ ከሞላ ጐደል የምችለውንና የማውቀውን በጽሑፍ አድርጌ መሄድ አለብኝ ብለው ተነሡ:: በዚህ መጽሐፍ ዝግጅት ነበር የሚደክሙት:: የዚያ ዝግጅት ይመስለኛል በመጨረሻ ጊዜ የጐዳቸው:: በድንገት ታመው በዚያው ቀኑ፤ ዐረፉ::

መልአከ ብርሃን ያነባሉ ይጽፋሉ:: ሁለቱም የእርሳቸው ነው:: የትም ሄዱ እቤትም ገቡ ሥራቸው መጽሐፍ ማንበብ ወይም መጻፍ ነው:: እረፍት የላቸውም:: እኔም በ፲፱፻፺፫ ዓ.ም በታተመው «የኢ ትዮጵያ እምነት በሦስቱ ሕግጋት» በሚለው መጽሐፌ መግቢያው ላይ ያንን መጽሐፍ ለመጻፍ ካነሣሣኝ ምክንያቶች አንዱ ከእሳቸው ጋር በጥ ብቅ መነጋገሬ ነው ብዬ ያስቀመጥኩት ነገር አለ::

ትምህርትና ሙያ እስከ ዕለተ ሞት አይቋረጥም ይባላል:: በእው ነት እኔን ብዙ መምህራን አስተምረውኛል:: ጥሬ ጥሬውን ያስተማሩኝ ልበላቸው:: መቼም ሰብስቦ እቤት ማግባት ብቻ አይደ ለም:: የገባውን ደግሞ ወደ ሰው ጉሮሮ እንዲደርስ እንዲገባ የሚያደርግ ሥራ ያስጠ ፈልጋል:: እህሉ አንድ ሴቱ አሥራ ሁለት ይባላል ከነተረቱ:: የሙያም





ሆነ የትምህርትን ነገር ከሊቃውንቱ በየጊዜው ማስተካከል ያስፈ ልጋል:: በዚህ ዓይነት ከጠቀሙኝ መምህራን ዋናው መልአከ ብርሃን ናቸው:: የሃይማኖቱን ትምህርት መልኩን ለይተው ጥርት አድርገው ደርዙን፣ ልዩነቱን፣ አቀራረቡን ሁሉንም ከእርሳቸው ነው ማጥናት የቻልኩት:: ስለ ምሥጢረ ሥላሴ፣ ምሥጢረ ሥጋዌ የሚመስለውን ሁሉ ዝምብዬ በዳሰሳ ያጠናሁትን ለይቼ እንዳውቀው ጣዕሙ እንዲ ጣፍጠኝ ያደረጉት ኅሊናዬንም እንድገዛ ያደረጉት መልአከ ብርሃን ናቸው::

መልአከ ብርሃን ጠንካራ እምነት ነበራቸው:: ታላቅ መንፈሳዊ የጸሎት ሰው ናቸው:: ምኅርካ ክርስቶስ የሚባለው ልጃቸው ታሞ ሞተ ተብሎ ቤተ ዘመድ ሁሉ ሕዝቡ ተሰብስቦ ሲያለቅስ ለቀብር ሲዘጋጁ እሳቸው በማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ ስምንት የተጻፈውን እያነበቡ አዝዝ በቃልከ ይሕየው ወልድዬ ልጄ እንዲድን በቃልህ እዘዝ ብለው እንባቸውን ሲረጩት ልጁ ተነሣ ይባላል:: ይኸው ልጅ አሁንም በሕ ይወት ይገኛል:: ዛሬ ትልቅ ሰው ነው::

ከመልአከ ብርሃን አድማሱ ጋር በአባትነት በመምህርነት ደረጃ ብቻ ሳይሆን በጓደኝነት ደረጃም እንነጋገር ነበር:: አንድ ነገር ሲመጣ ይሄንን እንዴት ታየዋለህ ይሉኛል:: እኔ የምሰጣቸውን አስተያየትና ሃሳብ ካመኑበት ይቀበላሉ:: ልክ ነህ እኔ አሳስቻለሁ ያንተን ተከት ዬአለሁ ይላሉ:: ቅርበታችን እስከዚህ ድረስ ነበር:: መኖሪያ ቤታቸው ጉለሌ ራስ ኃይሉ ሠፈር ነበር:: ጠቅላይ ቤተ ክህነት ሥራቸውን ሲ ሠሩ ይውሉና እኔም እዚያው ውዬ ስንወጣ ጨዋታችን አላልቅልን እያለ ተያይዘን በእግራችን ከጠቅላይ ቤተ ክህነት /አራት ኪሎ/ ጉለሌ ድረስ እንሄድ ነበር:: በእሳቸው ሞት በተለያየ አቅጣጫ ብዙ ጉዳት ደርሶብኛል:: በቤተ ክርስቲያን አንፃር ደግሞ ምን ማለት ይቻላል የማይተካ ሰው ነው የቀረው:: በሕይወቱም ሆነ በቤተ ክርስቲያን አገልግሎቱ ያንን የመሠለ ሰው መተካት አይቻልም:: በአገር አንፃርም ቢሆን ከፍተኛ አገልግሎት አበርክተዋል:: በከፍተኛ ፍርድ ቤት በዳኝነት ይሠሩ ነበር:: በሁሉም አቅጣጫ የተሟላ እኒህን የመሰለ ሰው ከየት ይገኛል::

መልአከ ብርሃን አድማሱ ጀምበሬ ለቤተ ክርስቲያን በአጠቃላይ ደግሞ ለኢትዮጵያ ያበረከቱትን አስተዋጽኦ ይኸ ነው ተብሎ ተዘርዝሮ የሚዘለቅ አይደለም። ከአንድ ሰው ሕዋሳት ቢጐድል የማይጐዳ የለም። እርግጥ ማባባስ ከመጣ እግዚአብሔርም መምህራኑን ዓይኖች ናችሁ ነው ያላቸው። ዓይን ማጣት ከባድ ነገር ነው። እንደ መልአከ ብርሃን ያሉ ርዕሶችን ማጣት ለቤተ ክርስቲያን ለሃገርም ጉዳቱ ያን ያህል ነው። ጭራሹን ሲታጡ ቀርቶ ደክመው ከቤት ሲውሉ ከሥራ ገበታ ቸው ሲለዩ እንኳን ይጐዳሉ። መማሩ ብቻ አይደለም። ለትውልድ ጠቃሚ የሆነን ነገር ጽፎ አዘጋጅቶ ማቅረቡ ራሱ ታላቅ ተግባር ነው። በሚፈለገው ጊዜ ለሚቀርብላቸው ጥያቄ ሁሉ አስፈላጊውን መልስ መስጠት ተቀባይ ማግኘት ይኼ ሁሉ የተሟላለት ሰው ከየትም አይ ገኝም። መልአከ ብርሃን ይኼ ሁሉ የተሟላላቸው ነበሩ። አስበው ማዘጋጀት የሚችሉ፣ ያዘጋጁትንም ለሰው ማቅረብ የሚችሉ፣ ያቀረ ቡትም ደግሞ በሰው ፊት ተቀባይነት ያለው ሰው ነበሩ።»

አለቃ አያሌው ታምሩ

«የአባቴን ታሪክ የማስታውሰውን ያህል በጽሑፍ እንዲቀርና ቅርስነት አግኝቶ ለትውልድ እንዲተላለፍ በማድረጉ ላይ የማስታው ሰውና የማውቀውን ያህል ለመናገር አጋጣሚውን ማግኘቴ ታላቅ ዕድል ነው። ሲሆን እኛ ራሳችን ተወላጅ ልጆቻቸው የምንደክምበት ጉዳይ ነበር። ግን ያ ሳይሆን ቀርቶ እንደዚህ ዓይነት ለሀገር ለቤተ ክርስቲ ያን የሚያስብ ማኅበር ሲገኝ ደግሞ እኛ ስለ አባታችን የምናውቀውን ያህል የመግለጽ ግዴታ አለብን። ይህንን ዕድል በማግኘቴም በጣም ደስ ይለኛል።

ምኅርካ ክርስቶስ አድማሱ ጀንበሬ እባላለሁ። መልአከ ብርሃን ሰባት ልጆች አፍርተዋል። እኔ የመጨረሻ ልጃቸው ነኝ። እኔ አባቴ በኖሩበት ሞያ ሳይሆን በተማርኩት የአካውንቲንግ ሙያ ዛሬ በአዲ ተርንት እያገለገልኩ እገኛለሁ።

መልአከ ብርሃን እኔ ሳውቅ ጀምሮ በቤት ውስጥ በጣም ትዕ ግሥተኛ ብዙ የማይቆጡ የማይናገሩ ሰው ነበሩ። በተለይ ደግሞ አሁን





ዲሞክራሲ ተብሎ እንደሚጠራው የእኩልነት መንፈስ በቤታችን ውስጥ በጣም የሠረፀ ነበር። የዚህ ምክንያቱ እሳቸው ናቸው። እኛ ልጆቹም ስናድግ በቤት ውስጥ ተጽዕኖ አልነበረብንም። ምናልባት ቁጣ ቢኖርም እንኳን በጊዜው ልንደርስበት የቻልነው ትምህርት ዳዊት፣ ውዳሴ ማርያም የመሰሉትን በምንማርበት ጊዜ እሳቸው የሚሉትን ሳን ቀበል ስንቀር ወይም ደግሞ ግድፈት በሚኖርበት ጊዜ ከሚያደርጉት ቁጣ በስተቀር በሌላው ኑሯችንና ሁኔታችን እኔ ሲቆጡ የማስ ታውስበት ጊዜ የለም። ሌላውም የቤተሰብ አባል የተቆጡበትን ጊዜ የሚያስታውስ አለ ብዬ አላስብም። ሁሉንም በእኩል ሚዛንና መንፈስ የማየት አቀባበል ነበራቸው።

መልአከ ብርሃን አድማሱ በቤተክርስቲያን ሊቅንታቸው አባትነታ ቸውና በመንግሥት አስተዳደር ውስጥ ያለባቸው ኃላፊነት በቤት ውስጥ የሚፈጥረው የተለየ ተጽዕኖ አልነበረም። ከልጆቻቸውም ሆነ ከቤተሰባቸው አባላት ጋር ቀርበው በነፃነት የመወያየት ችሎታ ያላ ቸው ነፃ ነበሩ። ይኸንን በሁለት ብከፍለው ጥሩ መልክ ሊኖረው ይችላል።

አንደኛው ጎጃም የብቸና ቅዱስ ጊዮርጊስ መልአከ ብርሃን በነበሩ በት በተለይም ቀደም ባለው ጊዜ በ፲፱፻፴፩ ዓ.ም ይመስለኛል /ጊዜ ውን በትክክል መናገር ባልችልም/ ቤተ ክርስቲያኑን ሲያስተዳድሩ በወ ቅቱ የቤተ ክርስቲያን አስተዳደር ራሱ በጉልት ገዥነት ደረጃ ስለነበረ ሃያ አራት አገሮች /አጥቢያዎች/ በብቸና መሪነት በተጨማሪ ለአስ ተዳደሩም ሆነ ለዳኝነቱ የደብሩ አለቃ ሓላፊነት ነበረባቸው። እሳቸ ውም ይኸንን ሁሉ አጠቃለው ይሠሩ ነበር። በዚያን ጊዜ ሕዝብ ይመ ለከታቸው የነበረው እንደ ማንኛውም አገረ ገዥ ስለነበረ የውጪው ሰው ጌቶች ነበር የሚላቸው። በቤተሰብም ውስጥ ሌላው ሰው የሚለ ውን ተከትለን ጌቶች ነበር የምንለው። በዚያን ጊዜ ሰውም ለእሳቸው የነበረው ከበሬታ በጣም ትልቅ ነው። እንደዛሬው የመንግሥት ሥራ ቸውን የሚያከናውኑበት የተለየ ቢሮ ስላልነበረ ችሎት የሚያስችሉበት ቦታ የተለየ ይሁን እንጂ ቢሯቸው ቤት ውስጥ ነው። በዚያን ወቅት ሁልጊዜም ለአስተዳደር ጉዳይም ሆነ ለዳኝነት ይመጣ የነበረውን ሕ ዝብ እናይ ነበር። ችሎት በሚያስችሉበት ጊዜ በትንሹ ከሠላሳ እና

አርባ ሰው በላይ በግቢው ውስጥ ይኖር ነበር:: ያን ጊዜ ሁሉ ነገር እርካሽ ነው:: እንደልብ ይገኛል:: እዚያ አደባባይ የዋለው ሰው ሁሉ ከእሳቸው ጋር ወደ ቤት ገብቶ ምሳ በልቶ ቡና ጠጥቶ ተጋብዞ ነበር የሚሄደው:: እሳቸው ዘንድ ለአስተዳደራዊም ሆነ ለዳኝነት ጉዳይ የሚመጣው በደጅ ጥናት እንዲንገላታ በፍጹም አይፈልጉም ነበር:: ወዲያውኑ ፍትሕ አግኝቶ ወደ መጣበት እንዲመለስ ያደርጋሉ::

አባታችን ወደ አዲስ አበባ ጠቅላይ ቤተ ክህነት ተዛውረው በመጡ ጊዜ ብቻና የነበረው ነገር ሁሉ ቤተሰቡን ተከትሎ ወደ አዲስ አበባ አልመጣም:: አብሮ የመጣው ቤተሰባዊው ፍቅርና መተሳሰብ ብቻ ነበር:: በቤት ውስጥ የሚደረገው ነገር ሁሉ በነፃነት ነበር:: ከገደብ የሚወጣ ነገር የለም:: ሁሉም ነገር ሥነ ሥርዓት አለው:: ሁሉ ነገር ሥነ ሥርዓት እስከተከተለ ድረስ በቤተሰቡ ላይ የሚደርስ ተጽዕኖና ገደብ አልነበረም:: እኔ የመጨረሻ ልጅ በመሆኔ በወቅቱ ሕፃን ብሆንም እንኳን ትንሽ ነው ሳይባል ገበታ አብሬያቸው እቀርብ ነበር:: በውይይትም ጊዜ ትንሽ ናቸው፣ ልጆች ናቸው ሳይባል የፈለግነውን ጥያቄ መጠየቅ እንችላለን:: በውይይትም ላይ በነፃነት እንሳተፍ ነበር:: ነፃ የአባትና ልጅ ቤተሰባዊ መቀራረብ ነበረን::

ጸሎት የሚያደርጉት ወንጌል ዘዮሐንስ ነው:: ሁልጊዜም አይቀርም:: ዳዊት አይታጐልም:: ሌሊት ተነሥተውም፣ በመንገድ ሲሄዱም ዳዊት ይደግማሉ:: እና ውዳሴ ማርያም ያደርሳሉ:: ከዚህ በፊት ፋሽስት ኢጣልያ ኢትዮጵያን በወረረበት ወቅት በተለይ በጸሎት የተወሰነበት ጊዜ ነበር:: በመንገድ ላይ ሲሄዱ ሁሉ ዳዊት እየደገሙ ነበር የሚሄዱት:: በዚሁ በጣላት ጊዜ ቅኔ እያስተማሩ ነበር ያሳለፉት:: እኔ የተወለድኩባት የዘረዘር የምትባል ቦታ አለች:: ከዲማ ወደ የዘረዘር በሚሄዱበት ጊዜ በሁለቱ መካከል ላይ ገድ የምትባል ሸጥ አለች:: እዚያ ሽፍቶች መንገደኛ እየጠበቁ ይዘርፋሉ:: ሌላም ከፍተኛ ጉዳት ያደርሳሉ:: አንድ የገበያ ቀን በዚያ መንገድ ብቻቸውን ሲሄዱ ሽፍቶች እየጠበቁ ይዘርፋሉ:: በመንገድ ላይ አንዲት ሴት ከኋላቸው መጥታ አባክህ ከአንተ ጋር ልሂድ ትላቸዋለች:: እኔስ እንደአንችው





ባዶ እጄን አይደለሁም ወይ ከምን አስጥልሻለሁ ይሏታል:: ሴትዮዋም ከአንተ ጋ ብሄድ ይሻለኛል በማለት አብራቸው መጓዝ ቀጠለች:: እሳቸው እንደተለመደው ዳዊት እየደገሙ ነው የሚጓዙት:: ከሴትዮዋ ጋር አብረው ሲሄዱ ከፊታቸው ይጓዙ የነበሩትን ነጋዴዎች ሽፍቶች አስቁመው ሲዘርፏቸው ይደርሳሉ:: እነዚያ ሽፍቶች ነጋዴዎቹን እየቀሙ በነበሩበት ጊዜ መልአከ ብርሃንን ያዩዋቸዋል:: ወዲያውኑ መጣብን ብለው ሽፍቶቹ የሚቀሙትን ትተው እየተሯሯጡ ወደ ጫካ ገቡ:: እሳቸውም ከሴትዮዋ ጋር በሰላም አለፉ:: ኃይላቸው ጠባቂያቸው ጸሎታቸው እንደነበረ ብዙዎች ይናገራሉ::

በጣልያን ጊዜ አገራቸው ዲማ ሄደው በኃዘንና በጸሎት ተወስነው ቅኔ እያስተማሩ በኖሩበት ጊዜ በብቻና አድባራት ሁሉ ምሕላ በማስያዝ ቆይተዋል:: ከብቶች ጥጃ ከላሟ እየተለያዩ ሕዝቡ እየተሰበሰበ በጾም በጸሎት ስለ አገር ነፃነት አምርረው ያለቅሱ ነበር:: በዚህም ጣልያን በተለይ በብቸና አውራጃ ብዙ ጊዜ የሽፍታ አገር ነው በአውሮፕላን ይደብደብ እየተባለ በእግዚአብሔር ጥበቃ ሳይፈጸም ቀርቷል:: የእምነታቸውን ጽናት አስመልክቶ እኔ ልጃቸው ብሆንም ብዙዎቹ በሥራም ሆነ በተለያየ ምክንያት የሚያውቋቸው ሁሉ ብዙ ይናገራሉ:: ለምሳሌ እኔ በወቅቱ ባላስታውሰውም በኋላ ሲነገር እንደምንሰማው የአራት ዓመት ልጅ እያለሁ /፲፱፻፴፩ ዓ.ም ይመስለኛል/:: በጠና ታመምኩ:: ታምሜ በነበረበት ወቅት እናቴም ሆነች ሌሎች ዘመድ ወዳጆቻችን ሁሉ ተስፋ በመቁረጥ በየጊዜው ሞተ ይሉ ነበር:: አንድ ቀን የባሰ ሁኔታ ተፈጠረ:: እንደነገሩኝ በዚያን ጊዜ እኔን ይዘው ከፊታቸው የጌታችንን ሥነ ስቅለት አድርገው ወንጌሉን ከደገሙ በኋላ እጅግ በጣም እንደሚቀርቡትና አጠገባቸው እንዳለ ሰው ንግግር ነበር የሚያደርጉት:: <እንዴ... ሃይማኖት ያለው ይድናል ብለሃል:: የዚያን የመቶ አለቃውን ልጅ እምነት ስለነበረው ነው ያዳንከው:: እኔስ እምነት አለኝ አይደለም ወይ....በምን ምክንያት ነው የእ ኔን ልጅ የምትገድለው?> ከእምነታቸው ጥንካሬ የተነሣ እንደዚህ ነበር ንግግራቸው:: በዚያን ጊዜ እዚያ ብቸና ግዛት እስላሞችም ይገኛሉ::

ብዙ እስላሞች ነበሩ:: እንግዲህ በዚያን ጊዜ መልአከ ብርሃን የብቸና
ሹም በመሆናቸው የሹም ልጅ ታመመ፤ ሞተ ሲባል ብዙ ሰው ወደ
ቤት ይሰበሰባል:: እስላሞቹም ሊጠይቁ መጥተው ነበር:: እሳቸ ውም
በጸሎታቸው <እነዚህ እኮ እስላሞች ናቸው:: አንተን ልጄን
ታድንልኛለህ ብዬ በፊታቸው ለምኜሃለሁ እና እነሱ ፊት እንዴት
ታሳፍረኛለህ?> ነበር የሚሉት:: የእናቴ አባት ደግሞ ቄስ ነበሩ::
በኋላ በምንኩስና ሕይወት የኖሩ ደግ ሰው ነበሩ:: በዚያን ጊዜ እሳቸው
ስለነበሩ አባቴን <ለምንድነው እግዚአብሔርን የምታስጨንቀው እሱ
ሠራው የሠራውን ይውሰድ ለምን ታስቸግረዋለህ?> እያሉ በአንድ
ወገን ይናገሯቸው ነበር:: ከዚያ በኋላ እንደነገሩን ሁለት ጊዜ ሞተህ
ነበር ነው የሚሉኝ:: በእሳቸው ጸሎት ተነሣሁኝ::

ይኸ ሁኔታ በተፈጸመ ጊዜ መልአከ ብርሃን በብቸና ይሾማሉ::
እርግጥ ብቸና ይወለዳሉ:: ነገር ግን ተወልደው ያደጉት ዲማ ስለነበረ
የዲማ ሰው ተብለው ነው በብቸና የሚታወቁት:: ስለዚህ የብቸና
ሰዎች እያሉ ከዲማ መጥቶ እንዴት ተሾመብን የሚል በወቅቱ የአካ
ባቢው ሰዎች ቅሬታ ነበራቸው:: እዚህ ላይ መቼም ሰዎች ነገና ሰዎቹ
<ይኸ ደብተራ በድብትርናው ነው ይሄን ሹመት ያገኘው> እያሉ
ያሚቸው ነበር። በኋላ የእኔን ከሞትኩ በኋላ በእሳቸው ጸሎት መነ
ሣቴን እዚያው አይተው የእምነታቸውን ጥንካሬ ካረጋገጡ በኋላ <ተሳ
ስተናል እኚህ ሰው ለካ ጻድቅ ኖረዋል> በማለት ተናገሩ:: ሕዝቡም
ከዚያ በኋላ በአክብሮት ይመለከታቸው ነበር:: እኔንም አሁንም ድረስ
ያን ጊዜ የነበሩ ሰዎች ባገኙኝ ቁጥር ሞቶ የተነሣው ልጅ ነው
የሚሉኝ::

አባቴ አዲስ አበባ ከመጡ በኋላ ጊዜያቸው ሁሉ ከሥራቸው ጋር
በማንበብና በመጻፍ የተጣበበና የተያዘ ነበር:: የሥነ ጽሑፍ ስሜቱ
አደረብኝ የሚሉት ከጠላት /የጣልያን ወረራ/ በፊት እሳቸው የሚ
ያውቋቸው ውዱ የሚባሉ ሰው ነበሩ:: እኚህ ሰው ጋዜጣ ላይ ጽፈው
ስማቸውን አነበብኩ አሉ:: <እሱ መጻፍ ከቻለ እኔስ ለምን መጻፍ
አልችልም?> የሚለው ሃሳብ ያደረብኝ ያን ጊዜ ነው ይሉ ነበር::





በማንበብ በኩል መጽሐፍ አይመርጡም:: የሃይማኖት መጽሐፍ ያዘወት
ራሉ:: የታሪክ መጻሕፍት፣ አልፎ አልፎ የሰዎች ግለ ታሪክ (Bibliog-
raphy) እና ልቦለድ መጻሕፍት ማንበብ ይወዳሉ::

መልአከ ብርሃን አዲስ አበባ በነበርንበት ጊዜ ዕረፍት ብለው
የተቀመጡበት ጊዜ ትዝ አይለኝም:: ፍርድ ቤት በሚሠሩበትም ጊዜ
ሆነ ጠቅላይ ቤተ ክህነት ሲሠሩ ጠዋት መሥሪያ ቤት ይመጣሉ፤
ሥራ ውለው ወደቤታቸው ይመለሳሉ:: ምሣ ወይም ራት ዘጠኝ ወይም
አሥር ሰዓት ላይ ከበሉ በኋላ ወደ ጽሕፈት ጠረጴዛቸው ሄደው ይቀ
መጣሉ:: ከዚያ በኋላ መኝታ ነው:: ምንጊዜም እረፍት አልነበራቸ
ውም:: እና በጣም ያነቡና ይጽፉ ነበር:: መጻሕፍቶቻቸውንም ያዘጋጁ
ት በዚህ ሁኔታ ነው:: ብዙ ሥራዎቻቸው በጠቅላይ ቤተ ክህነት
ይገኛሉ::

አንድ መሠረታዊ የሆነ አሳብ ነበራቸው:: ቤተ ክርስቲያንን የሚ
መለከት ነገር ከሆነ በጣም ክብር የሚሰጡትና የሚያስቡለት ጉዳይ
ነበር:: ራሳቸውን አሳልፈው የሚሰጡለት ነገር ነበር:: እና ካዘጋጇቸው
ውስጥ ለምሳሌ ልዑል ሣህለሥላሴ በሚያገቡበት ጊዜ የተክሊል ድር
ሰት ተፈለገ:: ከዚያም እሳቸው ሥርዓተ ተክሊልን በጥሩ ሁኔታ አዘጋ
ጅተው አቀረቡ:: ስሙም በቤተ ክርስቲያኒቷ እንጂ በራሳቸው ስም
እንዲሆን አይፈልጉም ነበር:: ብዙ ከማንበባቸው የተነሣ ነው ቤተ
ክርስቲያንን በመንቀፍና የሃይማኖት ኑፋቄን የሚመለከቱ መጽሐፎችን
የሚያገኙት:: በዚህም ምክንያት መልስ ሰጪ የሆኑ መጻሕፍትን ለማ
ዘጋጀት ችለዋል::

አባቴ በዲያሎግ /ውይይት/ ያምናሉ:: ይኸ እምነቴ ነው መደረግ
አለበት አይሉም:: እሳቸው እንደነገሩኝ ማስታወቂያ ሚኒስቴር የሚ
ሠሩ አንድ የቲዮሎጂ ዶክተር ካቶሊክ ነበሩ:: ይተዋወቁ ስለነበረ ውይ
ይት /ዲያሎግ/ እንዲያደርጉ ጠይቀዋቸው ሰውየው ሳይቀበሏቸው ቀር
ተዋል:: እኔ ልጅ ሆኜ በ፲፱፻፵፭ ዓ.ም ይመስለኛል:: በኢትዮጵያ
ሬዲዮ ጣቢያ በዐቢይ ጾም ማታ ማታ ያስተምሩ ነበር:: ያን ጊዜ መሣ
ሪያው /ቴክኖሎጂው/ ኋላ ቀር በመሆኑ በየቀኑ ማታ ማታ ራሳቸው

በአካል ሬዲዮ ጣቢያው ድረስ እየሄዱ ከዚያው ነበር የሚተላለፈው፡፡ እኔም አብሬአቸው ስለምሄድ ጨርሰው እስከሚወጡ ድረስ በጨለማው ውጪ ጠብቄአቸው ከዚያ በኋላ ከማስታወቂያ ሚኒስቴር ጉለሌ እቤታችን ድረስ በእግራችን እንሄድ ነበር፡፡ በዚህ ዓይነት የሰጡትን ትምህርት አሰባስበው ከአዘጋጁት በኋላ «ሐዲስ ሰውነት» ብለው በመጽሐፍ አሳተሙት፡፡ ከዚያ በኋላም እንደእነ «መድሎተ አሚን»፣ «ኰኲሐ ሃይማኖት» ያሉትን መጻሕፍት ጽፈ ዋል፡፡ በመጨረሻው ዘመናቸው «ዝክረ ሊቃውንት» የተባለውን መጽሐፍ በሚያዘጋጁበት ጊዜ በጣም ይጓጉ ነበር፡፡ የኢትዮጵያ ሊቃውንት ታሪክና ሥራ ተቀብሮ መቅረት የለበትም፡፡ እያሉ ያስቡ ነበር፡፡ የሊቃውንቱን ታሪክና ሥራ ማሰባሰቡን የጀመሩት ከብዙ ጊዜያት በፊት ነው፡፡ የከፍተኛ ፍርድ ቤት ዳኛ በሆኑበት ጊዜ በየአገሩ ሲዞሩ ዕድል አጋጠማቸውና የሚያገኟቸውን ሰዎች ሁሉ አምጡልኝ እያሉ ታሪካቸውን ሲያሰባስቡ ቆዩ፡፡ በዚህ ሁኔታ ዝክረ ሊቃውንትን አዘጋጁ፡፡ የመጀመሪያው ቅጽ /ቮሊዩም/ ሊያልቅ ሲል እሳቸው ዐረፉ፡፡

በዚያን ጊዜ አቡነ ቴዎፍሎስ ነበሩ፡፡ እኔን አስጠርተው መጽሐፉ የሚቀረው ዝግጅት ካለ እንዲያልቅና እንዲታተም ብለው አዘዙ፡፡ በአንድ ጥራዝ አለቀ፡፡ ከዚያ በኋላ አቡነ ቴዎፍሎስ <የሚቀጥለውም የመጽሐፉ ክፍል ተዳፍኖ መቅረት የለበትም ረቂቁን አምጥተህ ለሊቃውንት ጉባኤ ስጥ> ብለውኝ ረቂቁን ወስጄ አስረከብኩ፡፡ በመካከሉ በተፈጠሩ ችግሮች የመንግሥት ለውጥ አብዮት መጣ፡፡ አቡነ ቴዎፍሎስም ታሠሩ ለሞት በቁ፡፡ በእንዲህ ዓይነት ሁኔታ ሳይታተም ጊዜው አለፈ፡፡ በመጨረሻው ከብዙ ጊዜ በኋላ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሚገኘው የኢትዮጵያ ጥናት ተቋም በአነስተኛ ቅጂ /ኮፒ/ አሳተመው፡፡ ለሕዝብ የተዳረሰ ግን አይመስለኝም፡፡

መልአከ ብርሃን በሚጽፉበት ጊዜ እንግዲህ ሥራቸው በቤተ ክህነት ስለነበረ ገቢያቸውም ውስን ነበር፡፡ የምንኖርበትም ቤት ያን ያህል የሚያወላዳ ባለ መሆኑ የራሳቸው ጥናት ክፍል ወይም ጽ/ቤት በቤታቸው አልነበራቸውም፡፡ የሚጽፉትም ሆነ የሚያነቡት በሳሎን





ውስጥ ነው፡፡ የቤተሰብ ቤት ስለሆነ ሳሎን ያለውም ሰው ያወራል፡፡ ሥራውን ይሠራል፡፡ እሳቸው ዝም ብለው ሥራቸውን ይሠራሉ፡፡ ስለቦታ አይጨነቁም ነበር፡፡

መልአከ ብርሃን ለቤተ ክርስቲያን መብት በየአጋጣሚው ከመታገል ወደ ኋላ ያሉበት ጊዜ የለም፡፡ እኔ እንኳን ሕፃን ብሆንም የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የራሷን ሊቃነ ጳጳሳት መሾም አለባት በሚለው ክርክር ጊዜ የጎጃምን ሊቃውንት ወክለው ወደ አዲስ አበባ የመጡት ታላቅ ወንድሜን አስከትለው ነበር፡፡ ከዚያ በኋላ ሲያወሩ እንደሰማሁት በጣም ትልቅ ክርክር ነበር፡፡ በዚያን ጊዜ እጨጌው እጨጌ ገብረ ጊዮርጊስ ነበሩ፡፡ እሳቸው እንኳን ሳይቀሩ አሳቡን ተቃውመው ነበር፡፡ ነገር ግን በኋላ ፓትርያርክ የሆኑት ራሳቸው እጨጌ ገብረ ጊዮርጊስ /ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ባስልዮስ/ ናቸው፡፡ በዚያን ጊዜ ብዙ አባቶች ተቃውመዋል፡፡ ኢትዮጵያ የራስዋ ሊቀ ጳጳስ ይኑራት ማለትን ሃይማኖት እንደማፋለስ አድርገው ይቆጥሩት ነበር፡፡ ብዙ ትግል ተደርጎ ይኸው ፍሬው ለዚህ በቃ፡፡ ከእሱ በኋላ ደግሞ በ፲፱፻፶ዎቹ ውስጥ ፕሮቴስታንቶች የብሥራተ ወንጌል ሬዲዮ ጣቢያ እናቋቁም ብለው መንግሥትን ጠየቁ፡፡ ጉዳዩም ወደ ቤተ ክህነት ተመራ፡፡ ጉዳዩ ለቤተ ክህነት እንደቀረበ በወቅቱ የነበሩ አባቶች ሁሉ በቁጣ ተቃወሙ፡፡ ወዲያውኑ ስብሰባ ተቀመጡ፡፡ በስብሰባው ላይ መልአከ ብርሃን ይኸ ሬድዮ ጣቢያ ይፈቀድላቸውና ይከፈት፡፡ ግን ለእኛም የአየር ጊዜ ይሰጠንና እናስተምር፡፡ እነሱ አንድ ነገር ቢሉ እኛም በጥሩ ሁኔታ መልስ መስጠት ነው በማለት ተከራከሩ፡፡ በመጨረሻ ሃሳቡ ለንጉሠ ነገሥቱ ቀርቦ ሬዲዮ ጣቢያው ሲከፈት የአየር ጊዜም ለቤተ ክርስቲያን ተሰጠ፡፡ በቅድስት ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ተምሮ ማስተማር በሚል ትምህርተ ወንጌል በዚሁ የአየር ጊዜ ማስተማር የተጀመረው ያኔ ነው፡፡ መልአከ ብርሃንም በዚሁ ሬዲዮ ፕሮቴስታንቶቹ የሚያስተላልፉትን እሳቸው በጥሩ ሁኔታ መልስ እየሰጡ በማስተማር ብዙ ጊዜ አገልግለዋል፡፡ እንደውም በዚሁ በፕሮቴስታንቶቹ ሬዲዮ ጣቢያ በብሥራተ ወንጌል ከተለያዩ አቅጣጫዎች እጅግ ብዙ ጥያቄዎች

እየቀረቡላቸው የተሟላ መልስ በመስጠት ሰፊ ማብራሪያ በማቅረብ በራሳቸው በፕሮቴስታንቶቹ ሬዲዮ ጣቢያ ተጠቅመው ከፍተኛ ሥራ ሠርተውበታል:: በሚገባ አስተምረውበታል::

መልአከ ብርሃን በጣም ትዕግሥተኛ ነበሩ:: የሚናደዱበትን ጊዜ ወይም ተበሳጭተው አይቼ አላውቅም:: ይኸ ጠባያቸው ከልጅነታቸው ጀምሮ በወጣትነታቸውም የነበረ ነው ይባላል:: የሚያስቆጣ ነገር ቢያጋጥማቸውም ስሜታዊ ሆነው ወዲያውኑ የሚወስዱት እርምጃ አልነበረም:: አንድ እርምጃ ለመውሰድም ሆነ ለመወሰን በጣም ዝግተኛ ነበሩ:: እስከ ዕድሜያቸው መጨረሻ ድረስ ይሠሩ ነበር:: ያነቡ ይጽፉ መጻሕፍትን ያዘጋጁ ነበር:: በመጨረሻው የታመሙ ዕለት እንኳን ቀን ሲሠሩ ውለው «ዝክረ ሊቃውንት» የተባለውን መጽሐፍ በትኩረት ሲያዘጋጁ ውለው ሌሊት ስድስት ሰዓት አካባቢ ነው በድንገት /ስትሮክ/ የሞቱት:: መልአከ ብርሃን የመጠቀ አስተሳሰብ ነበራቸው::

በጣሊያን ጊዜ ይመስለኛል:: በዲማ በጣም የታወቁ አባ እውነቴ የሚባሉ መነኩሴ ነበሩ:: ዲማ ንዋያተ ቅድሳት የሚቀመጡበት ዋሻ ነበር:: መነኩሴውም በዚያ ዋሻ ነበር የሚኖሩት:: አንድ ቀን አባቴ

እርሳቸው ዘንድ ሄደው በነበረበት ወቅት... <ይሄ የአውሮፕላን ሥራ የጥበብ ይመስልሃል ወይስ የሰይጣን?> ብለው ጠየቋቸው:: መልአከ ብርሃንም <የኔታ ይኼስ የጥበብ ይመስለኛል÷ ለምሳሌ ቶፋ /የሸክላ ድስት/ ውኃ ይጣድበታል:: መግላሊት /ክዳን/ ከላይ አለው:: ውኃው በሚፈላበት ጊዜ መግላሊቱን ወደ ላይ ያነሣዋል:: ከዚያ ጋር ተዛምዶ ያለው ይመስለኛል::> ብለው መለሱላቸው:: መነኩሴውም እግዚአብሔር ይስጥህ ልጄ ተባረክ ብለው እንደመረቋቸው ይናገራሉ:: ምክንያቱም ከዚያ በፊት ሌሎችን ካህናት ሄደው ይኸንኑ ሲጠይቋቸው «የኔታ ይኸማ የሰይጣን ሥራ ነው» ብለው ይመልሱላቸው ነበር:: እና ብዙ ጊዜ አንድን የተለየ ወይም አዲስ ነገር ዝም ብለው አይቀበሉም:: ይመራመራሉ:: አመለካከታቸውም የቀደመ ነው::

መልአከ ብርሃን በዚያን ጊዜ ሁሉንም ተምረዋል:: ነገር ግን አውቃለሁ ብለው አይቀመጡም:: ቅኔውን በልጅነታቸው ተምረዋል::





ከተለያዩ መምህራን ቀጽለዋል:: መጻሕፍቱን ተምረዋል:: ሌሎቹንም የቤተ ክርስቲያኒቷን ትምህርት ተምረዋል:: ትምህርታቸው ግን ማብቂያ የለውም ነበር:: በዚያን ጊዜ በትልቅ የቤተ ክርስቲያን ሓላፊነትና ሥራ ላይ እያሉ ሊቅ ሆነው በሊቃውንቱ ዘንድ እየሄዱ ይጠይቁ ይመራመሩ ነበር::

እኔ የመጨረሻ ልጃቸው ብሆንም ቀደም ባሉት ጊዜያት አባታችን መልአከ ብርሃን ባለቤታቸውን /እናታችንን/ በተለይም ነፍሰ ጡር በሚሆኑበት ጊዜ እግራቸውን የሚያጥቧቸው እሳቸው ነበሩ:: ለባለቤታቸው የሚያደርጉት አክብሮትና ክብካቤ ለእኛም ለልጆቻቸው ታላቅ ትምህርት ሆኖናል::

*ምኀርካ ክርስቶስ አድማሱ*

ከሞት የተነሣው ልጃቸው

ምሕርካ ክርስቶስ ማለት «የክርስቶስ ምርኮ» ማለት ነው

*ምንጭ፡- ስምዐ ጽድቅ ጋዜጣ ታኅሣሥ ፲፱፻፺፰ ዓ.ም*

ምንጭ:-

- ⇒ መልአከ ብርሃን አድማሱ ጀንበሬ፣ ዝክረ ሊቃውንት ፲፱፻፷፫ ዓ.ም፣ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፣ አዲስ አበባ
- ⇒ የክቡር መልአከ ብርሃን አድማሱ ጀንበሬ የ40 ቀን መታሰቢያ መጽሔት፣ ጳጉሜ ፫ ቀን ፲፱፻፷፱ ዓ.ም ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፣ አዲስ አበባ
- ⇒ «ዜና ቤተ ክርስቲያን » ሐምሌ ፲፱፻፷፱ ዓ.ም